
ጣዮ ሕይወት

ዲጂታል መጽሔት

ቅጽ 1 ቁጥር 5 ጥር 2018 ዓ.ም.



የደብረ ገሊላ አማኑኤል ካቴድራል
አግዚአብሔር ምስሌነ ሰንበት ት/ቤት
የተዘጋጀ
የጥር 2018 ዓ.ም. ዕትም

01 ማውጫ

ነጋሪት/ ዝዜኑ/ ማረፊያ/ ዋኖቻችን/ ጎብረ ነገር / ለወራዙት/ ውሉደ አግናጥዮስ

ከመንበር የሚያወርድ ፍቅር — በዝግጅት ክፍሉ — 02

የወልደ እግዚአብሔር ጥምቀት — ዲ/ን ዶ/ር ዓለማየሁ ኢሳይያስ — 03

ወዴት ነህ — ዲ/ን ናትናኤል ሽዋንግዛው — 05

የዲያቆናት አለቃ ቅዱስ እስጢፋኖስ — ዲ/ን ሮቤል ወንድወሰን — 06

ቃና ዘገሊላ — በዝግጅት ክፍሉ — 07

ለጥምቀት ያልሆነ ልብ — አስተርአየ ገሃደ — 08

ጥር ሃያ ስምንት — ልድያ አቦወርቅ — 09

ዋና አዘጋጅ

- በትምህርት እና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል መጽሐፍ እና መጽሔት ዝግጅት ንዑስ ክፍል

አዘጋጅ

- ዲ/ን ሮቤል ወንድወሰን
- ልድያ አቦወርቅ
- ሜላት ክብረት
- ቅድስት ግዛቸው
- አስተርአየ ገሃደ
- ኢየኤል ግዛቸው
- ዕፀብ ታከለ

አርታኢ

- ጉባኤ አርትዖት ክፍል

ግራፊክስ ዲዛይን

- ዲ/ን ሮቤል ወንድወሰን (Architect)
- ራሔል የሺንጉስ

02 ከመንበር የሚያወርድ ፍቅር

እግዚአብሔር ቸርነቱን ለሰው ልጅ ካሳየበት እና የደግነቱን ልክ ካሳወቀበት ነገሮች ሁሉ ይህ ይልቃል። ሰው አክብሮ እና ለዩቶ የፈጠረው ፍጥረት ቢሆንም አስቀድሞ የሚያሰፈልገውን ነገር ሁሉ ያዘጋጀለት ከመሆኑም በላይ ውብ እና ሁሉ የሞላባት በሆነች የኤደም ገነት ያስቀመጠው መሆኑን አድንቀን ብናስብም ከሁሉ በላይ ግን እኛን የሚያስደንቀን የፍቅሩን ጥልቀት እና ስፋት አንረዳ ዘንድ የፈጠረውን ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ መገለጡ ነው።

አምላክ የሆነ አርሱ፤ ያለ አርሱ የተገኘ ነገር የሌለ የሚታየውንም የማይታየውንም የሠራ፤ በቃሉ ሰማዩን ያቆመ ብርሃንን ይሁን ብሎ የፈጠረ፤ የሰው ልጅ ከምድር አፈር ያበጀው፤ ያ ጠቢብ ችሎታው፤ ሰጪ የሌለው አርሱ ሰው ሆኖ ተገለጠ። ከዚህ በላይ ምን ያስደንቀናል? ምንም። ሁሉን ሙሉ አድርጎ የፈጠረው የሰው ልጅ ከሞላለት ይልቅ ጎድሎሳል የሚልን የጠላት ወሬ ወደ ጆሮው ላከና ልቡ ያልተሰጠውን የማይገባውን አምላክነት ሻተ። ያበጀውን መሆን ፈለገ የእግዚአብሔር ዙፋን ሊገዳደር አሰነው፤ በእንዲት ፍሬ ጣዕም የአምላክነትን መንበር የሚይዝ መሰለው፤ እናም ሳተ ከተሰጠው እጥፍ ይልቅ ተው የተባለው እንዲት በለስ ከአምላኩ ልትለየው እንደምትችል የመታዘዝ መንገዱ፤ አምላኩን የመከተያ ድልድዩ የአሺታው ማሕተብ መሆኗን ረሳ፤ አዩ ማለትን ለእንደበቱ ከለከለና የዘለዓለም ሽልማት የሆነውን የአምላኩን ልጅነት አጣ።

በፍቅር ይጠራው የነበረውን የአምላኩን ድምጽ ቁጣ ሆኖ አደመጠው፤ ጸጋው ተገፈፈ እርቃኑን ሆኖ እንዲት በለስ ዘለዓለማዊነትን ነሳችው። አምላኩ ግን ይተወው ዘንድ ፍቅሩ ከለከለው ቸርነቱ አገደው እናም አርሱን ሆኖ የጥፋቱን ዋጋ ሊከፍልለለት አባቱ ምትክ ሆኖ ተገለጠ። ይህ እንደምን ያለ የፍቅር ጥግ ነው፤ በእጁ የሠራውን ሥጋ መንሳት በፈጠራት ምድር ላይ ሰው ሆኖ እስከመታየት ያለ መውደድ እንደምን ያለ ነው? አበው እንደነገሩን በእውነት እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ያጸነበት ጥበቡ ይበልጣል።

አምላክ ሰው ሆነ ሰውም አምላክ ሆነ በእውነት በፍጹም ተዋሕዶ በሰማይ ከአባቱ ሳይጎድል በምድርም ሰውነትን ሳይተው ፍጹም የአዳምን በደል ደመሰሰለት። በእንዲት ብላቴና፤ በእንዲት የ15 ዓመት የቤተ መቅደስ አገልጋይ፤ እንዲት ሀርና ወርቅን የምታስሟማ ታናሽ አገልጋይ በአምላኳ ሐሴትን በምታደርግ በእንዲት የትህትና ምልክት በእንዲት ዝምተኛ ሴት ይሁንልኝ የሚል የይሁንታ ቃል በማጎጸር አደረና በምድር ተገለጠ። ሰው ሆይ አምላክህ ሰው ሆኖ ተገለጠ መላእክት በመንቀጥቀጥ ክንፋቸውን ከልለው በፊቱ የሚነጠፉለት ጌታ በግርግም ከእንስሳት ጋር በማርያም አቅፍ አየነው። ያለሚቋረጥ ስብሐት ምስጋናቸው በሆነ ሠራዊት፣ ቅዱስ የሚባል ጌታ ሠማይ የአግሩ መረገጫ ናት የተባለለት ንጉሠ ነገሥት በእንግዳ በተጨነቀች ከተማ ውስጥ መወለጃ ቦታ አጥቶ በበረት ተኛ። ይህንን መገለጥ ለእኛ ያሳየንን ጌታ የምታመልኩ ሁሉ ስለዚህ ነገር ዕለት ዕለት ዕፁብ ዕፁብ በሉ፤ የመገለጡ ነገር የመወለዱ ነገር ለእኛ አእምሮ ሁልጊዜ አዲስ፣ ሁልጊዜ ግሩም ነውና በኃጢያት ለመነከር የምትሮጠውን ሥጋችንን ይህ ፍቅር ያግዳት ዘንድ በመገለጡ ገስጿት። የከፈለልን ዋጋ በልባችን ሰሌዳ ተጽፎ ዕለት ዕለት ለጽድቅ የምንቆም ያድርገን።

03 የወልደ እግዚአብሔር ጥምቀት

በዲ/ን ዶ/ር ዓለማየሁ ኢሳይያስ



ጥምቀት የሚለው ቃል አጥመቀ (አጠመቀ ወይም ነከረ) ከሚለው የግእዝ ሥርወ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም መጠመቅ፣ መነከር፣ መደፈቅ፣ ውኃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ማለት ነው። ጥምቀት ከሌሎቹ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ ላይ የሚፈጸም ምሥጢር ሲሆን ያለ ጥምቀት ከሌሎቹ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መሳተፍ አይቻልም። ዮሐ 2÷1-41 በጥምቀት ከእግዚአብሔር በመንፈስ እንወለዳለን፤ የልጅነት ፀጋንም እናገኛለን። የነፍስ ድኅነትን ለማግኘትም በጥምቀት የእግዚአብሔርን ልጅነት ማግኘት ግድ ነው። (ማር 16÷16፤ ዮሐ 3÷5)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበትን ዕለት በታላቅ ድምቀት በየዓመቱ ጥር 11 ቀን እንደምታከብር ይታወቃል። የጥምቀት በዓል አከባበር የሚጀምረው ጥር 10 ቀን በጾም ሲሆን ይህም ዕለት ገሃድ በመባል ይታወቃል። ትርጉሙም መገለጥ ማለት ነው። ምክንያቱም ወልድ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ፣ በኋለኛው ዘመን ደግሞ ያለ አባት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ፣ ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኖ ተዋሕዶ ስለተገለጠልን እና በ30 ዓመቱ በባሕረ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ክብሩንና ጌትነቱን ስለገለጠልን ነው።

ጌታ የተጠመቀው በ5530 ዓ.ዓ በዘመነ ሉቃስ በዕለተ ማግሰኞ ጥር 10 ለ 11 አጥቢያ ከሌሊቱ በ10ኛው ሰዓት በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ባሕር 30 ዓመት ከ13 ቀኑ ነው። የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ የተፈጸመ አይደለምና፤ አስቀድሞ ትንቢት ተነግሮለታልና። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በትንቢት መነጽር ተመልክቶ "ባሕር አየች፤ ሸሸችም ፤ ዮርዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ።" (መዝ 113÷3) በማለት ስለ ጌታ ጥምቀት ትንቢት ተናግሯል። ዳግመኛም "አቤቱ ውኆች አዩህ፤ ውኆችም አይተውህ ፈሩ፤ ጥልቆችም ተነዋወጡ ውኆችም ጮሁ።" (መዝ 77÷16) በማለት ዘምሯል። ነቢዩ ሕዝቅኤልም (ሕዝ 36÷26) ስለ ጥምቀት እንዲህ ብሏል። "ጥሩ ውኃንም አረጭባችኋለሁ፤ እናንተም ትጠራላችሁ አዲስም ልብ አሰጣችኋለሁ።" በትንቢተ ሚክያስ ምዕ. 7 ቁ 19 ላይም "ተመልሶ ይምረናል ፤ ክፋታችንንም ይቀጠቅጣል፤ ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል።" የሚል ተጽፎ እናገኛለን።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዘመኑ የተጠመቀው የሰው ልጆች ሁሉ አባት የሆነው አዳም የ30 ዓመት ጎልማሳ ሆኖ በ40 ቀኑ አግኝቶ በኋላ ያጣትን ልጅነት ለማስመለስ ነው። እርሱ አምላክ ሲሆን በእደ ዮሐንስ መጠመቁ ደግሞ ትህትናውን ለመግለጥ ነው። ጌታ ወደ ዮሐንስ ሄዶ መጠመቁ ለእኛ ለምእመናን ሥርዓት ሊያስተምረን ስለወደደ ነው። ቅዱስ ቃሉ ከሚነገርባት፣ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ከሚፈተትባት፣ የክርስቶስ ማደሪያ ከሆነች ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ ተጠመቁ ሲለን ነው። ይህ ሥርዓት ባይሠራልን ኖሮ በየዘመኑ የሚነሱ መኳንንትና መሣፍንት አባቶች ካህናትን ቤታችን መጥታችሁ አጥምቁን ብለው በጠየቁ ነበር። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው ሁሉም ሰው በቀላሉ ማግኘት በሚችለው በውኃ ነው፤ ምክንያቱም ጥምቀት መዳንን ለሚሻ ለሁሉ የተሰጠች ናትና።

በተጨማሪም ጌታ ከሌሎች ውኆች ይልቅ የዮርዳኖስን ባሕር የመረጠበት ምክንያት አለው። ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን በጨለማ መጋረጃ ጋርዶ ለእኔ መገዛታችሁን ማረጋገጫ ጽፋችሁ ስጡኝ ብሎ በጠየቃቸው መሠረት "አዳም ገብረ ለዲያብሎስ" እና "ሔዋን እመቱ ለዲያብሎስ" የሚል ጽፈው ሰጥተውት ነበር። ዲያብሎስም ይህንን በሁለት እብነ ርኪም ቀርጾ አንዱን በዮርዳኖስ ሁለተኛውን በሲኦል ጥሎታል። ጌታ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁንና በዮርዳኖስ የተጣለውን የእዳ ደብዳቤያችን

04 የወልደ እግዚአብሔር ጥምቀት

እንደ ሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፋቶልናል። (ፊል 2÷12)። ጌታ ጥምቀቱን ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ ያደረገበትም ምክንያት ምሥጢረ መንግሥቱን (አንድነቱን ሦስትነቱን) ለመግለጥ ነው። ጌታ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ሲወጣ አብ በደመና ሆኖ "የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት" ብሎ የእግዚአብሔር አብ የባሕርዩ ልጅ መሆኑን መስክሮለታል። መንፈስ ቅዱስም በነጭ ርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ አርፎበታል። (ማቴ 3÷ 13-17)። ጌታ ጥምቀቱን በቀን ያላደረገበትም ምክንያት አለው። ይኸውም ጥምቀቱን በቀን ቢያደርገው ኖሮ አይሁድ ይህ የወረደው መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን መናኛ ርግብ ነው ይሉ ነበር ብለው የቤተክርስቲያን አባቶች ያስተምራሉ።

በዓለ ጥምቀት

በግሪክ "ኤጲፋንያ" ማለት፣ በግእዝ "አስተርእዮ" እንዲሁም በአማርኛ "መገለጥ" የሚል ትርጉም ይሰጠዋል። ከበዓለ ልደት ጀምሮ እስከ ጸመ ነነዌ መግቢያ ያለው ጊዜም በዚሁ ምክንያት ዘመነ አስተርእዮ ይባላል። በዘመነ አስተርእዮ አምላክ ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡን፣ በእደ ዮሐንስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ የአንድነትና የሦስትነት ምሥጢር መታወቁን እና በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ላይ በአመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት በሠርግ ቤት የመጀመሪያው ተአምር መፈጸሙን (ዮሐ 2÷1-11) ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ታስተምራለች፤ ለፈጣሪዋም ምስጋናን ታቀርባለች።

ጥር 10 በከተራ ዕለት ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ መጥምቁ ዮሐንስ ሄዶ በዮርዳኖስ ባሕር መጠመቁን ለማስረዳት ታቦታት ከመንበራቸው ወርደው እና በካህናት አባቶች ከብረው በዓሉ ወደሚከበርበት ቦታ በየሬዳዊ ዝማሬ፣ በእልልታ እና በሆታ ታጅበው ይጓዛሉ። በገጠር ሳሉት አብያተክርስቲያናት ታቦታቱ በወንዝ ዳር፣ እንዲሁም በከተማ ደግሞ ለከተራ በተዘጋጀላቸው ጊዜያዊ ማረፊያዎች እንዲያርፉ ይደረጋል። ሌሊቱን ካህናቱ በቅኔ ማኅሌት ሲያገለግሉ አድረው ጠዋት ላይ የቅዳሴው ሥርዓት በካህናት አባቶች መሪነት ይከናወናል። የቅዳሴው ሥርዓት እንደተጠናቀቀ የተከተረው ውኃ (መጠመቂያው ውኃ) በካህናት አባቶች ከተባረከ በኋላ ሕዝቡ ተረጭቶ ከበረከቱ ይሳተፋል። በዓሉን በተመለከተም ትምህርት ሲሰጥ ቆይቶ ታቦታቱ ካረፉበት ድንኳን ተነስተው በመጡበት አኳኋን በየሬዳዊ ዝማሬ፣ በሽብሸባ

አና በእልልታ ታጅበው ወደየአጥቢያቸው ይመለሳሉ። በዚህ ዕለት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና የሰንበት ትምህርት ቤት መዘምራን "ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መሬታዊ (ሰማያዊው በመሬታዊው እጅ ተጠመቀ)" በሚለው ያሬዳዊ ዝማሬ አና ለበዓሉ በተዘጋጁ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መዝሙራት እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ።

በመጨረሻም የጥምቀትን ምሥጢር የምናመሠጥረው፣ በዓሉንም የምናከብረው ከላይ እንደዘረዘርነው ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ለእኛ ለክርስቲያኖች የምትፈጽምልን የጥምቀት ሥርዓት ከክርስቶስ ጋር የሞቱም የትንሣኤውም ተካፋይ መሆናችንን የሚያስረዳ ነው። ምክንያቱም ተጠማቂው ከውኃ ውስጥ መግባቱ ከጌታ ጋር መሞቱን ያመለክታል። ይህንን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጽ "ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን እኛ ሁላችን በሞቱ እንደተጠመቅን ሁላችሁ ዕወቁ። በሞቱም እንመስለው ዘንድ ከእርሱ ጋር በጥምቀት ተቀበርን፤ እርሱ ክርስቶስ በአባቱ ጌትነት ከሙታን እንደተነሣ እኛም እንደርሱ በአዲስ ሕይወት እንኖራለን።" (ሮሜ 6÷3-4)። በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት አጥማቂው ካህን ተጠማቂውን ሦስት ጊዜ በውኃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ እንዲል ማድረጉ ጌታ ሦስት ቀንና ሌሊት በከርሠ መቃብር ማደሩን የሚያስረዳ ሲሆን ተጠማቂው በሦስተኛው ጊዜ ከውኃ መውጣቱ ጌታ መነሣዘ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳዩል ከመቃብር ለመውጣቱ ምሳሌ ነው። እንደዚሁ እኛ በጥምቀት የእግዚአብሔርን ልጅነት ያገኘን ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር እንደምንነሣ እንደ ቅዱስ ቃሉ እናምናለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍልን እንዲህ ብሏል። "በሞቱ ከመሰልነው በትንሣኤውም እንመስለዋለን።" (ሮሜ 6÷5) በዓሉንም ስናከብር በትንሣኤ ዘጉባዔ እርሱን መስለን በመነሣት እግዚአብሔር አምላክ እርሱ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ኑ የአባቴ ቡሩካን ብሎ በቀኙ ከሚያቆማቸው ወገን እንደሚደምረን በማመን ነው ።

የጥምቀት በዓልንም እንደሚገባ አክብረን የበረከቱ ተካፋይ እንድንሆን እግዚአብሔር ይርዳን።

05 ወዴት ነህ?

ዲ/ን ናትናኤል ሸዋንግዛው

አብ በደመና ሆኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ አስረድቶ፣ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ፣ እግዚአብሔር ወልድም በአካለ ሥጋ ተገልጦ አማናዊ ምሥጢረ ሥላሴን ያስረዳ ዘንድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠመቀ። በቀደመው ዘመን ውኃ ለጥፋት አንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም ብለው ለሚያስቡ ሰዎች ድንቅ ሥርዓት የተፈጸመበትን ጥምቀት ጌታችን ውኃን ቀድሶ መሠረታት "ተቀደሰት ማዩ በጥምቀቱ/ውኃ በጥምቀቱ ተቀደሰች" ቅዱስ ያሬድ (ድጓ) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኃላ ሳዩውል ሰያድር ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄዶ ጸመ ጸለየ፤ ዮሐንስም ጌታን ካጠመቀ በኋላ ለመከራ ተሳልፎ ሊሰጥ በወኅኒ ቤት ገባ...

አየህ ወዳጄ ከክርስቶስ ጥምቀት በኋላ የጽድቅ መንገድ የምትጀምርበት ምዕራፍ ነው። አንተ ወዴት እየሄድክ ነው? እንጀራ አበርክቶ ሲያበላቸው፣ ሲፈውሳቸው ተሰብስበው በኋላ በዕለተ ዐርብ ይሰቀል እንዳሉት፤ ከጥምቀቱ በኋላ ዓመታዊ ንግሥ ሲሆን አልያም ሥራ ስታጣ ወይም የክርስቶስን መልኩን ለማየት እንደሚሄዱት ሰዎች አዲስ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ፣ ትልልቅ ዝግጅቶች ሲዘጋጁ ወይም ስትታመም መጥተህ በቤተ ክርስቲያን የስቃይ ጊዜ ድንጋይ ከሚወረውሩት መሃል ልትሆን ነው? እውነት እልሃለሁ በዚህ መሆን ለኛ መልካም ነው። አዩ አኔ ደካማ ነኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን ልቀርብ አይገባኝም ትለኝ ይሆናል። እንደ አመንዝራ የምትታይ የኃጢአት ቀራጭ ብትሆንም፣ በኃጢአት ባህር ላይ መረብ (ሰውነትን) የምትጥል ቢሆንም ጌታ ሐዋርያው ሊያደርግህ ዝግጁ ነው። ዘማዊ ብትሆንም የእንባህን ሽቱ ትቀባው ዘንድ የምሕረት እጆቹ የተዘረጉ ናቸው።

ጸጸትህን ለአይሁድ ካህናት ከክርስቶስ መንገድ ተቃራኒ ለሆኑ ሰዎች አትንገራቸው፤ እርሱን ካንተ ልብ አውጥተው ሊማርኩህ አስቀድመው ለይሁዳ እንዳደረጉት ገንዘብን፣ ከልብ ያልሆነ ፍቅርን ይሰጡሃል፤ ለጊዜው ደስተኛ የሚያደርጉህ መጥፎ ቦታዎች ይወስዱሃል። ያን ጊዜ ክርስቶስን በተራ ምድራዊ ነገር ትሸጠዋለህ።

እኔን ምሰሉ ያለውን አምላክህን ተከትለህ ከእርሱ ጋር አብረህ ሂድ። ልብህንና አካልህን ገዳም ወደ ተባለ እርምሞ፣ እርጋታ ወዳለው ሕይወት ውሰደው። በዚያን ሰዓት ፈታኝ ዲያቢሎስ ቀርቦ ይፈትንሃል ወደ ረድም ተራራ ወስዶ የቀደመ ምድራዊ ደስታህን በሕልም፣ በሐሳብም ሁሉ ያሳይሃል። አሁን የቀረብከውን ጌታህን ክደህ እኔን ብትከተለኝ እንደቀድሞ በደስታ ትኖራለህ ይልሃል። ክርስትናህን ጊዜያዊ ነገር ሳታደርግ በአምነት ጸንተህ ዲያቢሎስን ድል ስትነሳ ያን ጊዜ ሊያገለግሉህ በሃይማኖት በምግባር ሊያበረቱህ እግዚአብሔር መላእክቱን ስላንተ ያዛል ክርስቶስን ስትመስል ሞቱን ብቻ ሳይሆን ትንሣኤውንም ክብሩንም ትካፈላለህ። "በሞቱም እንመስለው ዘንድ ከእርሱ ጋር በጥምቀት ተቀበርን፤ እርሱ ክርስቶስ በአባቱ ጌትነት ከሙታን እንደ ተነሳ እኛም እንደ እርሱ በሐዲስ ሕይወት እንኖራለን በሞቱ ከመሰልነውም በትንሣኤው እንመስለዋለን።" ሮሜ 6÷5

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

06

የዲያቆናት አለቃ ቅዱስ እስጢፋኖስ

ዲ/ን ሮቤል ወንደወሰን



በሐዋርያት ስብከት ቤተ ክርስቲያን ስትስፋፋ በትምህርታቸውና በተአምራታቸው ተስበው ወደ ክርስትና እምነት የተመለሱ ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች መሬታቸውንና ጥሪታቸውን በመሸጥ ያላቸውን ሀብት አንድ ላይ በማድረግ በኢየሩሰሌም የአንድነት ኑሮን ይኖሩ ነበር። በኅብረትም የሐዋርያት ትምህርትን በመስማትና በጸሎት ይተጉ እንዲሁም ማዕድን በመባረክ በጋራ ይመገቡ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስም "አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሯቸው" (ሐዋ 4÷32) በማለት ስለ አንድነታቸው ፍጹምነት ይነግረናል። ነገር ግን በቁጥር እየበዙ ሲመጡ በመካከላቸው በማዕድ ምክንያት ልዩነት ተፈጠረ። ከይሁዲነት ወደ ክርስትና የተመለሱ ክርስቲያኖች በምግብ ክፍፍል ወቅት ከግሪክ የመጡትን ይጸየፋዋቸው፣ በተለይ ባልቴቶቻቸውን ችል ይሉባቸው ስለነበር በማኅበሩ መካከል አለመስማማት ተፈጠረ። ይህም በሐዋርያት ዘንድ ተሰማ። ሐዋርያትም "የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ አይደለም" ሐዋ 6÷2 በማለት ማዕዱንና በውስጥ ያለውን አገልግሎት ያስተባብሩ ዘንድ ሰባት ሰዎች እንዲመረጡ የክርስቲያኑን ኅብረት ጠየቁ። ምዕመናኑም በአሳቡ ደስ ተሰኝተው መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ክርስቲያኖችን መረጡ። ሐዋርያትም እጆቻቸውን ጭነው ረድዕ ይሆኗቸው ዘንድ ዲያቆናት አድርገው ሾሟቸው።

ከእነዚህም ዲያቆናት መካከል በቅድስና ሕይወቱ ለክርስቲያኖች አብነት የሆነው ሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ ይገኝበታል። እስጢፋኖስ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "አክሊል" ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግእዝ በኋላም ወደ አማርኛ የመለሱት አባቶች በቀጥታ የግሪኩን እስጢፋኖስ የሚለውን ቃል ተጠቅመዋል። ቅዱስ እስጢፋኖስ ምንም እንኳ ስሙ የግሪክ ስም ይሁን እንጂ በትውልዱ አይሁዳዊ ነው። ወላጆቹ ይህንን ስም ሊሰጡት የቻሉት በፍልስጤም ጠረፋማ ከተሞች ይኖሩ ስለነበር የግርክ ባሕልና ቋንቋ ተጽዕኖ አድሮባቸው ይሆናል ተብሎ ይገመታል።

ቅዱስ እስጢፋኖስ በሐዋርያት ጥበቃ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ከአምላክ ዘንድ ባገኘው የማስተማርና የፈውስ ሀብት ያገለግል ነበር። በእርሱም ታላላቅ ተአምራት ይፈጸሙ ነበር። ስለዚህም ሕዝቡ ከፊት ይልቅ እጅግ እየበዛና በትምህርት እየጠነከረ መጣ። አይሁድም ይህን ተመልክተው በቅዱስ እስጢፋኖስ ላይ በቅናትና በጠላትነት ተነሡበት። ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ ባገኘው ጥበብና ኃይል እነርሱን በቃልም በድርጊትም ይቃወማቸው ነበርና ሊረቱት አልተቻላቸውም። ስለዚህም አግዚአብርሔርንና ሙሴን ሲሳደብ ሰምተነዋል፣ ሙሴ የሠራልንን ሥርዓት ይለውጣል፣ በዚህ ቤተ መቅደስና በሕጉ ላይ የስድብን ቃል ይናገራል፤ ይህንንም ቤተ መቅደስ የናዝሬቱ ኢየሱስ አፍርሶ ብሏል እያለ ያስተምራል እያሉ፣ ሕዝቡን፣ ሽማግሌዎችንና ጸሐፍትን በማናደድ ይዘው ከሸንጎ ፊት አቆሙት።

ቅዱስ እስጢፋኖስን በሸንጎ ፊት ባቆሙት ጊዜም ፊቱ ልክ እንደ መልአክ ፊት ሆኖ በርቶ ነበር። እርሱም ለተከሰሰበት ነጥብ መልስ ሰጠ። ከአብርሃም አስከ ክርስቶስ ለእነርሱ የተሰጣቸውን በረከት በመቃወማቸው ከተሰፋ ቃል አርቀው እንደተወገዱ ገለጠላቸው። ክርስቶስንም ባለመቀበላቸው ወቀሳቸው። በዚህም ምክንያት በቁጣ ተነሣስተው ከከተማ ውጭ በመውሰድ በድንጋይ ወግረው ገደሉት። ቅዱስ እስጢፋኖስ አይሁድ በድንጋይ እየወገሩት ሳለ ሰማያት ተከፍተው ክርስቶስን በአብ ቀኝ ቆሞ ተመለከተ። ይህንን ራእይ የክርስቶስን ትንሣኤን ለማይቀበሉት አይሁድ አሰምቶ ተናገረ፤ እነርሱ ከፊት ይልቅ በእርሱ ጨከኑ በድንጋይም ወገሩት። ነገር ግን ቅዱስ እስጢፋኖስ ጌታውን ክርስቶስን መስሎ ነበርና ልክ እንደ መምህሩ ክርስቶስ "አቤቱ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው" ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኾ ነፍሱን ሰጠ። በቤተ ክርስቲያንም ታሪክ ስለ ክርስቶስ መስክሮ ሰማዕትነትን የተቀበለ የመጀመሪያው ዲያቆን ሆኗል።


በደማስቆ መንገድ ላይ ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረ ሳውል በኋላም ቅዱስ ጳውሎስ ተብሎ ስያሜ የተሰጠው ሐዋርያ ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ በሚወግሩበት ወቅት በእርሱ ሞት ተስማምቶና ድንጋዩን በእስጢፋኖስ ላይ ያነሡትን የአይሁድ ልብስ ይጠብቅ የነበረ ብላቴና ነበር። ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ ከሆነ በኋላ የእስጢፋኖስን ቤተሰቦች አጥምቋቸዋል። ይህ ደግሞ ድንቅ ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ቅዱስ የመታሰቢያ ቀን በመስጠት ጥቅምት 17 የድቁና ማዕረግን በአነብሮተ ዕድ በሐዋርያት የተቀበለበትን፤ ጥር 1 ደግሞ ዕረፍቱን ታስባለች።

የቅዱስ እስጢፋኖስ ጸሎትና በረከት ረድኤትና ምልጃ በሁላችን ላይ ለዘለዓለሙ ጸንቶ ይኑር! አሜን!

07 ቃና ዘገሊላ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በጥር 12 ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ በተደረገ ሠርግ ቤት ያደረገውን ተአምር በማሰብ በዓልን ታደርጋለች። ጌታችን ከጥምቀቱ በኋላ በዶኪማስ ሠርግ ቤት ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም እንዲሁም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ታጋብዘ በነበረበት ጊዜ ለእንግዶች ወይን ጠጅ አለቀባቸው።

በዚህም ጊዜ "እናቱ ጌታችን ኢየሱስን የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም" አለችው። ጌታችን ኢየሱስም "እንቺ ሆይ ካንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም" አላት። እናቱም ለአሳላፊዎቹ "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" አለቻቸው። በዚህም እንደ አይሁድ ልማድ የሚያነጹባቸው ስድስት የድንጋይ ጋኖች ነበሩ። ከእነርሱም እያንዳንዱ ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር። ጌታችን ኢየሱስም "ጋኖቹን ውኃ ሙሏቸው" አላቸው፤ እስከ አፋቸውም እስከ ላይ ሞሏቸው። አሁንም ቀዱና ወስደውም ሰጡት። አሳዳሪውም ያን የወይን ጠጅ የሆነውን ውኃ ቀምሶ አደነቀ፤ ከወዴት እንደመጣም አላወቀም፤ የቀዱት አሳላፊዎች ግን የወይን ጠጅ የሆነውን ያን ውኃ ያውቁ ነበር። ውኃውን የሞሉ እነርሱ ነበሩና። አሳዳሪውም ሙሽራውን ጠርቶ "ሰው ሁሉ መልካሙን የወይን ጠጅ አስቀድሞ ያጠጣል፤ ከጠገቡ በኋላም ተርታውንም ያመጣል፤ አንተ ግን መልካሙን የወይን ጠጅ እስከአሁን አቆየህ" አለው። ጌታችን ኢየሱስም በቃና ዘገሊላ ያደረገው የተአምራት መጀመሪያ ይህ ነው፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርትም አመኑበት። (ዮሐ 2÷1-11)



ከበዓሉ በረከት ያሳትፈን፤ አሜን!

08 ለጥምቀት ያልሆነ ልብ . . .

በአስተርአየ ገሃደ

በኢትዮጵያ ምድር ጥር ሲጠባ ምድሪቱ በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩ ቀለማት የምትሞሸረው ለበዓለ ጥምቀት ነው። ጥምቀት ከዘመነ አስተርአዮ ታላላቅ በረከቶች አንዱ ሲሆን፣ በውስጡ ጥልቅ ምሥጢራትንና ማራኪ ክዋኔዎችን አቅፎ የያዘ፣ በአማኙም ሆነ በጎብኚዎች ዘንድ በጉልህ የሚታወስ የአደባባይ ድምቀት ነው።

ጥምቀት የወጣቶች ነው የሚባለው አብዛኛው የበዓሉ ተሳታፊ፣ አድማቂና አገልጋይ የቤተ ክርስቲያን ተስፋ የሆኑት ወጣቶች በመሆናቸው ነው። በገጠርም ሆነ በከተማ የጥምቀት ዝግጅት ገና በዓለ ልደት ሳይቃረብ በወጣቱ መንፈስ ውስጥ ይጀምራል። የአብነትና የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የጥምቀት ቀለም የሳቸውን የሬዳዊ ዜማዎችና መዝሙራትን ሲያጠኑ፣ በየአጥቢያው የሚገኙ መንፈሳዊ ማኅበራትና የአካባቢው ወጣቶች ደግሞ ታቦታቱ በሚያልፉባቸው መንገዶች ላይ ስለሚደረጉ ዝግጅቶች መምከር ይጀምራሉ።

በማኅበራትና በሰንበት ትምህርት ቤቶች ያልታቀፉ፣ የአገልግሎት ድርሻ ያልተሰጣቸው ወጣቶች እንኳ ሳይቀሩ "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" የሚለውን ጥልቅ ሀገራዊ ብሂል አብነት አድርገው፣ በዓሉን አምረውና ተውበው ለማክበር ይዘጋጃሉ። ጥምቀት የአደባባይ በዓል እንደመሆኑ፣ ወጣቱ የባህል ልብሱን ለብሶ የሚታይበት ነው። በገጠሩ ባህልና በቆየው ባህላዊ ትውፊት መሠረት በዓሉ የመተጫጨና የትዳር አጋር የመፈለጊያ ዕድል የሚያገኝበትም ወቅት ነው። ጎበዛዝቱ ለሚወዷት ኮረዳ ሎሚ በመወርወር ምላሿን የሚጠብቁበትና ለቃና ዘገሊላ የሚቀጣጠሩበት እንደሆነም ማስተዋል የጥምቀት በዓልና የወጣቶችን ትስስር ያሳየናል።

ሆኖም ግን ይህ ለጥምቀት የሚውለው የውርዛቄ ልብ በሁለት ጎራ የተከፈለ ነው። በአንድ በኩል በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት በዓለም አደባባይ በመንበርከክ "ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይንበርከክ" (ፊል 2÷10) እያሉ በመመስከር በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ ያለነቀፋ ያለን አገልግሎት ሲያሰባስቡ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለዝሙትና ለመዳራት በር በሚከፍቱ አለባበሶች፣ ከመጠን ባለፈ መጠጥና በዓለማዊ ዘፈኖች ውስጥ በመጥፋት የበዓሉን ቅድስና የሚፈታተኑ ሁኔታዎች ይስተዋላሉ።

በተለይም በቡድን እየተከፋፈሉ በሙዚቃ እና በቁማር የምዕመኑን ልብ ትቶት ወደመጣው ዓለም የሚያሸፍቱ ማኅተብ ያሰሩ ወጣቶችን መመልከት፣ በስካር መንፈስ ተነሳስተው አላስፈላጊ ቃላትን የሚሰናዘሩና ለጠብ መጋበዝ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ከመሆን ባሻገር ቤተ ክርስቲያንን ባል የሚያስውል፣ ስም አስለጣፊ ተግባር ነው። ከምንም በላይ ግን ውድ የሆነው የክርስቶስ መቅደስ የሰው ልብ አለአግባብ የሚረክስበት መሆኑ ነገሩን አሳዛኝ ያደርገዋል።

ነገር ግን በዓለ ጥምቀትን በቤተ ክርስቲያን ዐይን ከተመለከትነው ከወንጌሉ፣ ከዝማሬው እንዲሁም ከዚያም አልፎ ከአያንዳንዱ ሥርዓት ለወጣትነታችን ስንቅ የሚሆን ትምህርትን የሚሰጠን ሆኖ እናገኘዋለን። የተወሰኑትን እንመልከት፡-

ጥምቀትን እንደ መለወጫ በዓል፡- የጥምቀት በዓልን ስናስብ የምናነሳው መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ከምድረ በዳ እየሰበከ የመጣው ቃል "መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" የሚለውን ያለፈውን ዘመን እንድንተውና በልባችን መለወጥ እንድንታደስ የሚጠይቀውን ቃል ነው። በበዓለ ጥምቀት ከካህናት አባቶቻችን ይምሮ ሁላችንም የቀደመውን ልብሳችንን ለውጠን በአዲስ ወይም በንጹሕ ልብስ በመዋባችን ውስጥ የጥምቀት በዓል ስለመለወጥ አንዳች ነገር ይነግረናል፡

ጥምቀት እንደ ትህትና በዓል፡- ቅዱሱን ሕያው አምላክ በፍጡሩ ይጠመቅ ዘንድ በባህረ ዮርዳኖስ ያስገኘው ነገር ቢኖር ትህትና ነው። ፈጣሪ በፍጡሩ እጅ በመጠመቅ ከትህትናው እንማር ዘንድ እኔን ምሰሉ አለን። በበዓሉም ላይ እንደምናየው በቤተ መቅደስ በፍጹም ክብር የሚቀደስበት ቅዱስ ታቦት ወደ ባህረ ጥምቀቱ ወርዶ በድንኳን/ በመቃኞ ወይም ወደ ጊዜያዊ ማረፊያ የሚወርደው፣ እርስ በእርስ ሲገናኙ ለሰላምታ እጅ የሚነሳሱት ስለ ነገረ ትህትና ነው።

ጥምቀት ክርስቶስን እንደመምሰያ በዓል፡- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ከክርስቶስ ጋር እንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን" (ሮሜ 6÷4) እንደሚል ምሥጢረ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር በሞቱና በትንሣኤው የምንተባበርበት ሲሆን በዓለ ጥምቀት ደግሞ ይህ ምሥጢር በተግባር/በአርአያነት የተመሠረተበት ዕለት ነው። ክርስቶስን መምሰል የክርስቲያኖች ትልቁ ግብና ዋና ዓላማ ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ 12÷1 ላይ እንደሚናገረው ወጣቶች ስንሆን በጉብዝናችን ወራት ፈጣሪያችንን ክርስቶስን ልናስብ ይገባል። ማሰባችን ደግሞ ግቡ እርሱን በመምሰል እንደ እርሱ ትህትናን፣ መልካምነትን፣ ፍቅርን ገንዘብ እንድናደርግ፣ በሕይወታችን ውስጥም ለቃሉ በመታዘዝ መንግሥቱን እንወርስ ዘንድ ይገባል። የበዓሉ አከባበርም የሚነግረን ይህንኑ ነው። በከተራ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ በትህትና ለመጠመቅ የሄደውን እርሱን በማሰብ አብረነው ከየአድባራቱ ወደ ባህረ ጥምቀቱ እንወርዳለን። በእኩለ ሌሊት ለተጠመቀው ክርስቶስ ልጆች ሆነን ተቆጥረናልና ወደ ባህረ ጥምቀቱ በመሄድ እንጠበላለን። በኋላም ከዮርዳኖስ በመመለሱ አምሳል ወደየየ አድባራቶቻችን እንመለሳለን። በዓለ ጥምቀት በጥር ወር የሚከናወን መንፈሳዊ አገልግሎት በሕይወታችን ሙሉ ይገለጥ ዘንድ ነጋሪ መካሪ መንገድ ነው።

09 ጥር ሳያ ስምንት

በልድያ አቦወርቅ

ልጆች እግዚአብሔር አምላካችን ምን ያህል እንደሚወዳችሁ ታውቃላችሁ? አምላካችን እግዚአብሔር እናን የሚወድበት መጠን እናን ከምናስበው በላይ ነው። እግዚአብሔር የማይለካውን ፍቅሩን ዕለት ዕለት በተለያየ መንገዶች ይገልጥልናል። በሚያደርጋቸው እያንዳንዶቹ ነገሮች ፍቅሩን የምንረዳ እናም ከሚያስደንቁን ነገሮች መካከል አንዱ የጌታችን ልደት ነው። የሚወደን አምላካችን ሰማይና ምድር የማይችለው ኃያል ንጉሥ ሆኖ ሰለ እርሱ ግን በትህትና ከብቶች በሚያድሩበት በረት ተወለደ። ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት በባርነት ለተያዙ ከባርነት ነጻ ሲያወጣቸው፣ ለሚታመኑበት ሁሉ ኃይል እየሆናቸው ጠላቶቻቸውን ሲበታትንላቸው፣ ለሚታዘዙት ሞገስ ሲሆናቸው፣ በጉድጓድ የተጣሉትን ከእንስሳት እየታደገ ሲያወጣቸው፣ የግፍ ግፍ ለደረሰባቸው መመኪያ ሲሆናቸው ያየነው አምላክ አሁን ደግሞ በሥጋ ተገለጠ።

ልጆችዬ መልካሙ አባታችን ቅዱስ አማኑኤል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በዚህ ምድር እያስተማረ በነበረበት ጊዜ የሰው ልጆችን እጅግ የሚወድ ነውና ሲያስተምር ሕዝቡ ሊረዳበት በሚችለው ምሳሌ እየመሰለ፣ ድሆችን ሳይንቅ፣ ሕጻናትን እያቀረበ፣ ብዙ ገቢረ ተአምራትንም እየሠራ ሰዎችን ከነበረባቸው ድውይ፣ ችግርና እክል ሁሉ እያላቀቃቸው ነበር። የሚያስተምራቸው ሰዎችም ሲራቡ እጅግ በጣም ያዝንላቸው ስለነበረ በመንገድ እንዳይዝሉ ይመግባቸው ነበር። የማቴዎስ ወንጌል ላይ እንደምናነበው በ7 እንጀራ እና በጥቂት ዓሣ ሴቶችና ሕጻናትን ሳይጨምር 4ሺ ወንዶችን በቸርነቱ አበርክቶ መግቦ ከበቡት ምግብ ደግሞ 7 ቅርጫት ተርፎ ነበር። ታዲያ በመጽሐፈ ስንክሳር እንደተጠቀሰው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ተአምር ያደረገበትን ዕለት ሁልጊዜ የጥር ወር በገባ በ28ኛው ቀን ታስበዋለች። ዓመታዊ በዓሉም በደብራችን በደብረ ገሊላ አማኑኤል ካቴድራል ይከበራል።

በኃጢአት ምክንያት ከገነት የወጣውን የሰውን ልጅ ሲመለከት በመራራት ወደ ገነት ሊመልሰው ብሎ ምድር ድረስ የመጣ አምላክ እንደምን ያለ ነው? ልጆቹ በሲኦል ውስጥ እንዳይሰቃዩ ብሎ በመስቀል ላይ የተሰቃየ አምላክ እንዴት ያለ ነው? ሲጠፋ ዙፋኑን ትቶ መጥቶ የሚፈልገው አባት ያለው፣ መራቡን አይቶ የሚያዝንለት፣ ከእግር እግሩ ተከትሎ ሲደክመው በሚሄድበት ሁሉ የሚረዳው፣ የሚደግፈው የሚመካበት አምላክ ያለው ልጅስ እንደምን የታደለ ነው?

"ጌታ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ሕዝቡ ከእኔ ጋር አስከ አሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ። በመንገድም እንዳይዝሉ ጦማቸውን ላሰናብታቸው አልወድም አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም ይህን ያህል ሕዝብ የሚያጠግብ ይህን ያህል እንጀራ በምድረ በዳ ከወዴት እናገኛለን? አሉት። ጌታ ኢየሱስም ስንት እንጀራ አላችሁ? አላቸው። እነርሱም "ሰባት ጥቂትም ትንሽ ዓሣ" አሉት። ሕዝቡም በምድር ላይ እንዳቀመጡ አዘዘ። ሰባቱንም እንጀራ ዓሣውንም ይዞ አመሰገነ። ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠ። ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ። ሁሉም በሉና ጠገቡ። የተረፈውንም ቁርስራሽ ሰባት ቅርጫት ሙሉ አነሱ። የበሉትም ከሴቶችና ከልጆች በቀር አራት ሺህ ወንዶች ነበሩ።" ማቴ 15÷32

አማኑኤል አምላካችን ጣዕመ ፍቅሩን ያሰድርብን!
አሜን!